# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## ፕላንና ልማት ቢሮ

## የአዲስ አበባ ከተማ ገጸ-ምድራዊ ፕላን አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር

## የአሰራር መመሪያ ቁጥር 179/2017

ግንቦት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ለየአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሥራ ላይ ያለውን መዋቅራዊ ፕላን ለማስተግበር የሚያግዙ ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላኖችን እና የጸደቁ ሌሎች ዝርዝር ፕላኖችን ለማዘጋጀት እና የፕላን ትግበራ ሥራው በተገቢው ወደ መሬት ለመውረድ እንዲቻል የፕላን አፈፃፀም ክትትል፣ ቁጥጥር የሚደረግበት የህግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤

የፕላን አፈፃፀም ክትትል፣ ቁጥጥር፣ ግምገማ እና የፕላን ኦዲት ሥራን በየደረጃው ባሉት የፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈፃሚ ተቋማት ያላቸውን የፕላን አተገባበር ሂደት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል አሰራር በማስፈለጉ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 16(2) (ሠ) እና አዋጅ ቁጥር 52/2009 አንቀጽ 39(3) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ የገጸ ምድራዊ ፕላን አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር አሰራር መመሪያ ቁጥር 179/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፕላንና ልማት ቢሮ ነው፤
   2. **"ክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት** ’ማለት የክፍለከተማ ፕላንና ልማት ጽህፈት ቤት ማለት ነው፡፡
   3. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መዋቅራዊ ፕላን አዋጅ ቁጥር 52/2009 ነው፤
   4. **‘ደንብ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ፕላን ዝግጅት፣ አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 130/2014 እና እንደተሻሻለው 181/2017 ነው፤
   5. **"የሩብ ዘመን ፕላን ማሻሻል ወይም ማሻሻያ"** ማለት መዋቅራዊ ፕላኑ ጸድቆ ወደ ትግበራ ከገባበት ጊዜ አንስቶ የሁለት ዓመት ተኩሉን ካጠናቀቀ በኋላ የሚከናወን በመዋቅራዊ ፕላኑ አንድ ክፍል ወይም ክፍሎች ላይ በአዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚከናወን ፕላን ማስተካከያ ወይም የማጣጣም ሥራ ነው፤

6. **"የመካከለኛ ዘመን ፕላን ማሻሻል ወይም ማሻሻያ"** ማለት መዋቅራዊ ፕላኑ ጸድቆ ወደ ትግበራ ከገባበት ጊዜ አንስቶ ባለው አምስት ዓመት ጊዜ ካጠናቀቀ በኋላ የሚከናወን በመዋቅራዊ ፕላኑ አንድ ክፍል ወይም ክፍሎች ላይ በአዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚከናወን የፕላን ማስተካከያ ወይም የማጣጣም ሥራ ነው፤
7. **"ፕላን ግምገማ"** ማለት በየደረጃው የተዘጋጁ ፕላኖች በተዘጋጀላቸው ስልታዊ እቅድ መሰረት መፈፀም አለመፈፀማቸውን በመስክና በቢሮ መረጃዎችን በማሰባሰብ የመተንተንና በአተገባበር ላይ የታዩ ጥንካሬወችንና ክፍተቶችን በመለየት ለቀጣይ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ሥራ መፍትሄ ማመላከት ነው፤
8. **"የፕላን ኦዲት"** ማለት የፕላን ትግበራ በታሰበለት አግባብ መከናወኑን እና ሁሉም የተተገበሩ ቦታዎች በአግባቡ ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑንና አለመሆን ለማረጋገጥ በቢሮ ውስጥ፣ በመስክ፣ በሚሰበሰብ መረጃ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ከቢሮም ከመስክም በሚሰበሰብ መረጃ፣ በተለያዩ መንገዶች በሚገኝ ጥቆማ እና በመሳሰሉት መረጃዎች ላይ በመነሳት የሚከናወን የማጣራት ሥራ ሲሆን ከሚገኘው ውጤት በመነሳት ፕላን በሚጥሱ አካላት ላይ ተጠያቂነት የሚሰፍንበት አሰራር ነው፤
9. በአዋጁ እና በደንቡ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች በዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡
10. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ አዋጁና ደንቡ ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

የመመሪያው ዓላማዎች ፡-

1. በከተማው የጸደቁ ፕላኖች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤
2. በከተማው ውስጥ የተቀናጀና የተቀላጠፈ የፕላን አፈፃፀም ክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ ስርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ ተጠያቂነት ማረጋገጥ ነው፡፡

6. <u>የፕላን አፈፃፀም ክትትል እና ቁጥጥር ስልቶች</u>

መዋቅራዊ ፕላን እና ፕላኑን ለማስተግበር የሚዘጋጁ ዝርዝር ፕላኖችን የሚተገበረው እና

የአፈፃፀም ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት የሚከተሉትን ስልቶች በመጠቀም ይሆናል፡-

1. በየደረጃው ያሉ የጸደቁ ፕላኖችን ፕላን አፈፃፃም ክትትል ማድረግና ግብረ-መልስ በመስጠት፣
2. የፕላን አፈፃፀም ክትትል ሪፖርት መሰረት በማድረግ በተለዩ ችግሮች ላይ በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት ወይም እንዳስፈላጊነቱ የፕላን አፈፃፀም ቁጥጥር በማደረግና የተጠያቂነት አሰራር ስርዓት መዘርጋት እና እንዲተገበር ማድረግ፤
3. የፕላን አፈፃፀም ግንዛቤ መፍጠር እና የአሰራር ጥራት ኦዲት ማድረግ፣
4. ገጸ ምድራዊ ፕላን አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ፤
5. ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ጉዳዮች በመዘርዘር ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የፕላን አፈፃፀም ክትትል እና ቁጥጥር

# አሰራር ስርዓት እና አተገባበር

7. የመረጃ ምንጮች አጠቃቀምና አሰባሰብ

   1. ፕላን ፈፃሚ እና አስፈፃሚ አካላት ለቢሮው ወይም ለክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤቶች በደንቡና በዚህ መመሪያ መሰረት የሚላኩለትን መረጃዎች በሰነድና በኤሌክትሮኒክስ ቅጅ በማድረግ ለክትትልና ቁጥጥር ሥራው መላክ ያለባቸው ሲሆን የሚላኩትም መረጃዎች፡-
      ሀ) ለልማት የሚተላለፉ የሽንሻኖ ፕላኖች፣ መብት የተፈጠረባቸው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት (ሶፍት ኮፒ በሲዲ)፣ ቤዝ ማፖች፣ በ1988 ዓ.ም ጂ.አይ.ኤስ መረጃ እና በሌሎች መንገዶች የባለቤትነት መብት የተፈጠረላቸው መሆኑን በመግለጽ፤
      ለ) የተሰጡ የህንፃ የግንባታ ፍቃዶች፣ የመሰረተ ልማት ግንባታ ፈቃዶች፣ የመጠቀሚያ ፈቃዶች እና እንደአስፈላጊነቱ የማስታወቂያ ፈቃዶች፤
      ሐ) ዝርዝር የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መስመሮችና የማከፋፈያ ጣቢያ ዲዛይኖች፤
      መ) የአረንጓዴ መሰረተ ልማቶች ዝርዝር ዲዛይኖች፤
   2. ከተቋማት የሚላኩ መረጃዎች መዋቅራዊ ፕላኑ በተዘጋጀበት መስመር ካርታ ቤዝ ማፕ መሰረት ተደራጅተው መላክ ይኖርባቸዋል፤
   3. ተቋማት የሚልኳቸው መረጃዎች መዋቅራዊ ፕላኑ በተዘጋጀበት መስመር ካርታ መሰረት ተደርጎ ቤዝማፑ ተወራርሶ እና ተደራጅቶ መላክ አለበት፤

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት መረጃውን አደራጅተው የማይልኩ ተቋማት መረጃው ተቀባይነት የማይኖረው እና የተሰጠውም አገልግሎት በቢሮው በኩል የማይወራረስ ሲሆን በሚደረግ ኦዲት እና ቁጥጥር ስራ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፤

5. ቢሮው በማንኛውም አካል በሚቀርብለት ጥቆማ፣ አቤቱታ እና የፍርድ ቤት ትእዛዝ እና የመሳሰሉትን እንደ መረጃ ይጠቀማል፤

6. ቢሮው የመስክ ጉብኝት በማድረግ የሚሰባሰቡ መረጃዎችን ለፕላን አፈፃፀም ክትትል፣ ቁጥጥር፣ ክዋኔ ኦዲት እና ፕላን ትግበራ ግምገማ ሥራን ያከናውናል፤

7. ቢሮው በሚያሰባስበው መረጃ እና ማስረጃ መሰረት የፀደቀ ፕላን በተሟላና በውጤታማነት እንዲፈፀም መደረግ አለመደረጉን በሚመለከት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

8. ማንኛውም ፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈፃሚ ተቋም በደንቡ፣ በዚህ መመሪያና ሌሎች ሕጎች መሰረት አገልግሎት የሰጠባቸውን መረጃዎች አገልግሎቱ በተሰጠ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለቢሮው ወይም ለክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤቶች እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

## 8. ገጸ ምድራዊ ፕላን አፈፃፀም ክትትል አሰራር

ገጸ ምራዊ ፕላን አፈፃፀም ክትትል ሥራዎች በሚከተሉት አግባብ መከናወን ይኖርባቸዋል፡-

1. ከፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈፃሚ ተቋማት የሚላኩ የፕላን መረጃዎች፣ ከመስክ የሚሰበሰቡ የፕላን መረጃዎችን የማደራጀት ሥራ ይሰራል፤
2. በተሰጡ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ሶፍት ኮፒ በሲዲ) በተመረጡ የኤሌክተሮኒክ ሚዲያዎች አማካኝነት፣ የግንባታ እና የመጠቀሚያ ፍቃዶች፣ እንዲሁም በተዘጋጁ የሽንሻኖ ፕላኖች በተወራረሱ ቤዝማፖች ላይ የፕላን አፈፃፀም ክትትል ሲደረግ በሚከተሉት ሁኔታዎች መከናወን ይኖርበታል፡-
   ሀ) የተላኩት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቤዝማፖች በየትኛው ዓ.ም የመሬት መረጃ እንደተስተናገዱ መረጃውን የሚልከው አካል በግልጽ ሊያሳውቅ ይገባዋል፤
   ለ) የጸደቀው ፕላን ቀድሞ በነበረ ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲዘጋጅ እና ሌላው ደግሞ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚዘጋጀው

ቀድሞ በተጠና ፕላን ላይ ሲዘጋጅ የተዘጋጀው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየትኛው አግባብ እንደተዘጋጀ በግልጽ ለይቶ መላክ አለበት፤

ሐ) ከፕላን ፈፃሚው ተቋም የተላኩት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቤዝማፖች በ1988 ዓ.ም በተዘጋጀው የጂ.አይ.ኤስ መረጃዎች የተስተናገዱ ከሆኑ ፕላኑ በይዞታው ላይ የመጣበት እንደሆነ ስለሚታሰብ በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ላይ ያለው የፕላን ተቃርኖ ተመላክቶ በቤዝማፕ ላይ ይደራጃል፤ከፕላን አንፃር ታይቶ ትክክለኛነቱን የማረጋገጥ ሥራ በሚሰራበት ወቅት እንዳለ በቤዝማፕ ይደራጃል፤

መ) በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቤዝማፕ ላይ የፕላን ተቃርኖ ተብሎ ተለይቶ በተመላከተው ቦታ ላይ የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት አይቻልም፤ የግንባታ ፈቃድ መስጠት የሚቻለው በፕላን ተቃርኖ ከተመላከተው ቦታ ውጭ ባለው ትክክለኛ ቦታ ላይ ብቻ መሆን አለበት፤

ሠ) ከ1988 ዓ.ም የጂ.አይ.ኤስ መረጃ ከሚስተናገዱ ይዞታዎች ውጭ ባሉ በተለያዩ መንገዶች በሚሰጡ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቤዝማፖች ላይ ምንም አይነት የፕላን ተቃርኖ መኖር የለበትም፣ የፕላን ተቃርኖ ተመላክቶ የሚገኝ ከሆነ የፕላን ጥሰት ስለሚሆን ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፤

ረ) የመዋቅራዊ ፕላኑ ከመጽደቁ በፊት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው ሆነው ፕላኑ ከጸደቀ በኋላ በስም ዝውውር፣ የመጠቀሚያ ፈቃድ እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለሚጠይቁና በአዲስ መልክ የምስክር ወረቀቱ የሚሰጣቸው ከሆነ መረጃው ሲላክ መዋቅራዊ ፕላኑ ከመጽደቁ በፊት የነበረው የመጀመሪያው የምስክር ወረቀት እና ቤዝማፕ መረጃ አብሮ መላክ አለበት፤

ሰ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ረ) መሰረት የተላከው መረጃ ፕላን ከመጽደቁ በፊት ምንም አይነት የፕላን ተቃርኖ የሌለው ከሆነና በአዲስ የጸደቀው ፕላን ላይ ሲታይ የፕላን ተቃርኖ የሚኖረው ከሆነ በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ላይ የፕላን ተቃርኖው ተመላክቶ ሲመጣ እንደፕላን ጥሰት አይወሰድም፤

ሸ) ፕላን ፈፃሚ ተቋሙ የሚልከውን የግንባታ ፈቃድ መረጃ በ2003 ዓ.ም የመስመር ካርታ ላይ አደራጅቶ መላክ ስለሚኖርበት በዚሁ አግባብ የተደራጀ መሆኑን ማረጋገጥ፤

ቀ) በኤሌክትሮኒክስ መረጃ የተላከውን እና በሰነድ የተላከውን መረጃ ተመሳሳይ መሆናቸውን እና የመዋቅራዊ ፕላን ስታንዳርዶች ተጠብቀው የተፈቀዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

በ) ከመዋቅራዊ ፕላኑ፣ ከአካባቢ ልማት ፕላኑ እና በሌሎች በህግ ከጸደቁ ዝርዝር ፕላኖች ጋር በማመሳከር የትንተና ሥራ መስራት፤

ተ) የፕላን ስታንዳርድን ጠብቆ የተፈቀደ ሆኖ ከተገኘ ወደ ቤዝማፕ እንዲካተት ይደረጋል፤

ቸ) ከፕላን ጋር የማመሳከር ስራው ሲሰራ የፕላን ጥሰት የተፈጸመ ሆኖ ሲገኝ የፕላን ጥሰቱን አይነትና መጠን በዝርዝር ሊያስረዳ የሚችል ግብረ-መልስ ለፕላን ፈፃሚ ተቋሙ እንዲደርሰው ይደረጋል፤

ኀ) የፕላን ፈፃሚ ተቋሙም የተሰጠውን የማስተካከያ ግብረ-መልስ ተቀብሎ የማስተካከል እና በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት የተስተካከለውን መረጃ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ የመላክ ግዴታ ስላለበት በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት መስተካከሉን ለማረጋገጥ የፕላን ቁጥጥር ሥራ ይከናወናል፤

ኘ) ይህን ተስተካክሎ የተላከውን መረጃ ጸድቀው በስራ ላይ ካሉት ፕላኖች እና ከማጠቃለያ ሰነዱ ላይ ካለው የከተማ ፕላን አሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶች፣ ደረጃዎች መመሪያ መሰረት ትክክለኛነቱን የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፤

አ) ከፕላን ጋር የማረጋገጡ ሥራ ሲሰራ የፕላን ጥሰት ያለበት ከሆነ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፤

ከ) የፕላን ጥሰቱን አይነትና መጠን ሊያስረዳ በሚችል መልክ የማስተካከያ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

ወ) የፕላን ፈፃሚ ተቋሙ በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ማስተካከያ በማድረግ መልሶ የመላክ ግዴታ አለበት፤ በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት መስተካከሉን የቁጥጥር ሥራ ይሰራል፤

3. የግንባታ ፈቃዶችን የፕላን አፈፃፀም ክትትል ሥራ ሲከናወን በሚከተሉት መሰረት ይከናወናል፡-

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ የሚላከው የግንባታ ፈቃድ መረጃ በ2003 የመስመር ካርታ( መዋቅራዊ ፕላኑ በተዘጋጀበት መስመር ካርታ) ላይ አደራጅቶ መላክ

የተቋሙ ግዴታ ስለሆነ በዚሁ አግባብ የተደራጀ መሆኑን ማረጋገጥ፤

ለ) በኤሌክትሮኒክስ መረጃ የተላከውን እና በሰነድ የተላከውን መረጃ ተመሳሳይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

ሐ) የመዋቅራዊ ፕላን ስታንዳርዶች ተጠብቀው የተፈቀዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

መ) ከመዋቅራዊ ፕላኑ፣ ከአካባቢ ልማት ፕላኑ እና በሌሎች በህግ ከጸደቁ ዝርዝር ፕላኖች ጋር በማመሳከር የትንተና ሥራ መስራት፣

ሠ) የፕላን ስታንዳርድን ጠብቆ የተፈቀደ ሆኖ ከተገኘ ወደ ቤዝማፕ እንዲካተት ይደረጋል፤

ረ) ከፕላን ጋር የማመሳከር ስራው ሲሰራ የፕላን ጥሰት የተፈጸመ ሆኖ ሲገኝ የፕላን ጥሰቱን አይነትና መጠን በዝርዝር ሊያስረዳ የሚችል ግብረ-መልስ ለፕላን ፈፃሚ አካሉ እንዲደርሰው ይደረጋል፤

ሰ) የፕላን ፈፃሚ አካሉ የተሰጠውን የማስተካከያ ግብረ-መልስ ተቀብሎ የማስተካከል እና በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት የተስተካከለውን መረጃ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ የመላክ ግዴታ ስላለበት በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት መስተካከሉን ለማረጋገጥ የፕላን ቁጥጥር ሥራ ይከናወናል፤

ሸ) ተስተካክሎ የተላከውን መረጃ ጸድቀው በስራ ላይ ካሉት ፕላኖች እና ከማጠቃለያ ሠነዱ ላይ ካለው የከተማ ፕላን አሰራር ደንቦች ሙያዊ ልምዶች ደረጃዎችና መመሪያ መሰረት ትክክለኛነቱን የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፤

4. የፕላን የማረጋገጡ ሥራ ሲሰራ የፕላን ጥሰት የተገኘበት ሆኖ የማስተካከያ እርምጃ ከተወሰደ በኋላ የፕላን ጥሰቱን አይነትና መጠን ሊያስረዳ በሚችል መልክ የማስተካከያ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

5. የፕላን ፈፃሚ አካሉ በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ማስተካከያ በማድረግ መልሶ የመላክ ግዴታ አለበት፤በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት መስተካከሉን የቁጥጥር ሥራ ይሰራል።

## 9. <u>የመጠቀሚያ ፈቃድ ፕላን አፈፃፀም ክትትል ማድረግ</u>

1. የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጠው ግንባታ መረጃ ከፕላን ፈፃሚ አካሉ ሲላክ በ2003 ዓ.ም በተነሳው የመሰመር ካርታ (የመዋቅራዊ ፕላኑ በተዘጋጀበት መስመር ካርታ)

ላይ የተደራጀ ቤዝማፕ ወይም የግንባታ ፈቃድ ማስረጃ አብሮ መላክ ይኖርበታል፤

2. የመጠቀሚያ ፈቃድ የፕላን አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ሥራው ሲሰራ የምንከተለው አግባብ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሰጥ በመሆኑ የስራ ፍሰቱ በሚከተለው መሰረት ይፈፀማል፡-

   ሀ) የተላከው መረጃ ትክክለኛ ቦታው ላይ የሚያርፍ መሆኑን፤

   ለ) የግንባታ ፈቃድ ያለው መሆኑን፤

   ሐ) በተፈቀደው የግንባታ ፈቃድ መሰረት ግንባታው የተጠናቀቀ መሆኑን ከመስክ በሚሰባሰብ መረጃ የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፤

3. የፕላን ጥሰት የተገኘበት ከሆነ ለፕላን ፈፃሚው አካል የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ የተገኘውን የፕላን ጥሰት በግልጽ በማብራራት ግብረ-መልስ ይሰጠዋል፤

4. ፕላን ፈፃሚው አካል በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ወስዶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ በማስተካከልና የተስተካከለውን መረጃ በድጋሚ የመላክ ግዴታ አለበት፤

5. በመዋቅራዊ ፕላኑ ላይ የተቀመጡ የህንፃ ውስጥ የተሽከርካሪ ማቆሚያና የመኖሪያ ቤት ምጣኔ ስታንዳርድ በየጊዜው የመቀያየር ተግባር ሊከናወን የሚችልበት አግባብ ስለሚኖር የመጠቀሚያ ፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ሥራው ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ መከናወን አለበት።

10.<u>የመሰረተልማት ፕላን አፈፃፀም ክትትል ሥራ</u>

1. የመሰረተ ልማት ፕላን አፈጻጸም ክትትል ሥራ የሚከናወነው እንደ መሰረተ ልማቱ ዓይነት ይሆናል፤
2. የጸደቁ የመሰረተ ልማት ዲዛይኖችን በማሰባሰብ ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ በቤዝማፕ የማደራጀት ሥራ ይሰራል።

11.<u>ስለ ፕላን አፈፃፀም ክትትል ስራ</u>

የመንገድና ትራንስፖርት፣ የአረንጓዴ መሰረተ ልማት፣ የደረቅ ቆሻሻ ማሰባሰቢያና ማስወገጃ ቦታዎችን እንዲሁም የካባና የማዕድን ማውጫ ቦታዎች ፕላን አፈፃጸም የክትትል ሥራ የሚሰራው በሚከተለው ሂደት ይሆናል፡-

1. የፕላን አፈፃፀም ክትትል የሚደረግባቸውን ቦታዎች መለየት፤

2. ዝክረ-ተግባር ማዘጋጀት፤
3. ቸክሊስት ማዘጋጀት፤
4. የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ ማዘጋጀት፤
5. ለስራው የሚያስፈልጉ የፕላን መረጃዎችን ማሰባሰብ፤
6. የመስክ መረጃዎችን ማሰብሰብ፤
7. በመስክ የተሰባሰቡ መረጃዎችን የማደረጃት እና መተንተን፤
8. ወደ ሶፍት ኮፒ ቀይሮ በቢሮ ውስጥ ካለው የፕላን መረጃ ጋር በማነፃፀር የሚታዩትን የፕላን ጥሰት ችግሮችን መለየት፤
9. የፕላን አፈፃጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣በውይይት ማዳበር፤
10. በተለዩ የፕላን ጥሰቶች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት የጋራ ማድረግ፤
11. የተለዩ የፕላን ጥሰቶችን ለሚመለከተው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድባቸው በግብረ-መልስ ማሳወቅ።

12. **የፕላን አፈፃፀም ክትትል ሥራን በማጠናቀቅ ሪፖርት ስለማዘጋጀት**

1. በማንኛውም ደረጃ የተደረገ የፕላን አፈፃፀም ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ሪፖርት ይዘጋጃል፤
2. በሂደት በተለዩ የፕላን ጥሰቶች ላይ ከሚመለከታቸው የፕላን ፈፃሚ አካላት ጋር የጋራ ውይይት በማድረግ የፕላን ጥሰት መፈፀሙን የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝ ከተደረገ በኋላ የተፈፀመውን የፕላን ጥሰት የፕላን ፈፃሚ አካሉ ማስተካከያ ማድረግ ይኖርበታል፤
3. የጋራ መግባቢያ ውይይት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባለው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የተፈጸመው የፕላን ጥሰት አስተካክሎ ለቢሮው ሪፖርት እንዲያቀርብ በቃለ-ጉባኤ ላይ በመፈራረም የፕላን አፈፃፀም ክትትል ሥራው መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

13. **በፕላን አፈፃፀም ቁጥጥር አሰራር**

ፕላን አፈፃፀም ቁጥጥር ስራ ሲከናወን የሚከተሉት አሰራሮች ሊተገበሩ ይገባል፡-

1. የፕላን አፈፃፀም ክትትል በማድረግ የተለዩ የፕላን ጥሰቶች በሦስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ የፕላን ጥሰቱን የፈፀመው ፕላን ፈጻሚ አካል የፕላን ጥሰቱን ማስተካከሉን ለማጣራት በድጋሚ የፕላን አፈፃፀም ቁጥጥር ስራ ይከናወናል፤
2. በፕላን አፈፃፀም ክትትል ወቅት የተለዩ የፕላን ጥሰት መረጃዎች የተገኙባቸው

ቦታዎችን የመስክ ጉብኝት በማድረግ መረጃውን የማሰባሰብ ሥራ መስራት፤

3. በፕላን በአፈፃፀም ክትትል ወቅት በተቀመጠው የፕላን ጥሰት ማስተካከያ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተስተካክለው የሚገኙ ከሆነ በፎቶግራፍ እና በቪዲዮ በተደገፈ መረጃ ሪፖርት ይዘጋጃል፤
4. የፕላን አፈፃፀም ቁጥጥር በሚደረግበት ወቅት የተፈጸመው የፕላን ጥሰት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማስተካከያ ያልተደረገበት ሆኖ ሲገኝ የፕላን ጥሰቱን የፈጸመውን ፕላን ፈፃሚ አካል ወይም አስፈፃሚ አካል በህግ ተጠያቂ ለማድረግ ጥሰቱ በህግ ከጸደቀው መዋቅራዊ ፕላንም ሆነ እሱን ለማስተግበር በሚዘጋጁ ዝርዝር ፕላኖች ጋር ያለውን ልዩነት ሪፖርቱ ማሳየት አለበት፤
5. የፕላን ጥሰቱን መጠንና አይነት በማያሻማ መንገድ ማስረጃ በማሰባሰብ በፎቶ፣ በቪዲዮ፣ በንድፍ እና ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን በአባሪነት የሚይዝ የፕላን አፈፃፀም ቁጥጥር ሪፖርት መዘጋጀት ይኖርበታል፤
6. በተከናወነው የፕላን አፈፃፀም ቁጥጥር ሥራ ላይ የተዘጋጀውን ሪፖርት የፕላን ጥሰቱን የፈጸመው የፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈፃሚ አካል ተጠያቂ የሚሆንበትን ውሳኔ ለማስወሰን ለቢሮ ኃላፊው ቀርቦ ውሳኔ እንዲያገኝ ከተደረገ በኋላ ወደ ህግ አካላት እንዲተላለፍ ይደረጋል።

14. <u>የፕላን አፈፃፀም ስርፀት</u>

የፕላን አፈፃፀም ስርፀት ሥራዎች ሲከናወኑ በሚከተሉት መሰረት መሆን ይኖርበታል፡-

1. የመዋቅራዊ ፕላኑን እሳቤዎች፣ የማስፈጸሚያ ዝርዝር ፕላኖችን፣ የህግ ማዕቀፎች እና ስታንዳረዶች ከግምት ውስጥ በማስገባት መስራት፤
2. በፕላን ትግበራ ክትትል፣ ቁጥጥር እና የፕላን ክዋኔ ኦዲት ላይ በሚለዩ የፕላን አፈፃፀም ችግሮች በክህሎት ክፍተት የተፈጠሩ በሚሆንበት ወቅት እንደየባህሪያቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መስራት፤
3. በተለዩ ችግሮች ላይ የተሰጠውን የፕላን አፈፃፀም ግንዛቤ ስርፀትን በመከታተል ውጤት ማምጣቱን የማረጋገጥ ስራ መስራት፡፡

15. <u>የፕላን ክዋኔ ኦዲት</u>

1. የፕላን አፈፃፀም ጥራትን ለማረጋገጥ እንዲቻል፣ የተወሰኑ አካባቢዎችን ናሙና በመውሰድ የአፈፃፀም ክዋኔ ኦዲት ሥራ በቢሮው በሚከናወንበት ጊዜ ማንኛውም ፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈፃሚ አካል ያከናወነውን የሥራ

መረጃ የወረቀትና ኤሌክትሮኒክ ቅጂዎችን የማስረከብና ለክዋኔ ኦዲት ሥራው ተባባሪ የመሆን እንዲሁም በተሰጠው ግብረ-መልስ መሠረት የማስተካከል ግዴታ አለበት፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የተደረገው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ይዘጋጃል፣
3. የፕላን ጥሰት የማሰተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፤የአፈፃፀም ችግር የተገኘበት አካል ተጠያቂ ይሆናል፣
4. እንደአስፈላጊነቱ በየስድስት ወሩ በወረደ እና በሚወርድ የሳተላይት መረጃ በሚሰራ የክዋኔ ኦዲት ሥራ መሠረት በከተማው የተገነቡ እና የሚገነቡ ግንባታዎችን ከተሰጡ የግንባታ ፈቃዶች ጋር በማነፃፀር የፕላን አፈፃፀም ያለበት ደረጃ እንዲለይ በማድረግ የፕላን ጥሰት ከተገኘ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

16.<u>የፕላን ክዋኔ ኦዲት ቡድን ባለሙያዎች ሊያሟሏቸው ስለሚገቡት ሁኔታዎች</u>

የፕላን ክዋኔ ኦዲት ቡድን ባለሙያዎች የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. በሙያዊ ሥነ-ምግባርና በሕግ በተሰጠ ስልጣን የኦዲት ስራን ማከናወን፤
2. ባለሙያዎች በከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም ላይ በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸው መሆን፤
3. የኦዲት ስራው ሂደት ላይ ቀና አመለካከትና ታማኝነት ያለው ሆኖ መገኘት፤
4. የኦዲት ስራን በኃላፊነት ስሜትና ስታንዳርድን በመከተል ማከናወን፤
5. ከማናቸውም አድልዎ፣ ከጥቅመኝነትና ከአላስፈላጊ አሉታዊ ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ማከናወን፤
6. በተቀመጠው ጊዜና በጥራት ስራን ማከናወን፡፡

17.<u>ስለከተማ ፕላን ክዋኔ ኦዲት ስልቶችና ቴክኒኮች</u>

ከተማ ፕላን ክዋኔ ኦዲት የሚከተሉትን ስልቶችና ቴክኒኮችን ይጠቀማል፡-

1. የኦዲት ስራ መርሀ-ግብር ማዘጋጀት፤
2. የኦዲት ማድረጊያ መስፈርት ወይም ቼክሊስት ማዘጋጀት፤
3. የፕላን ሰነዶችን መመርመር፤
4. በፕላኑ የተተገበሩትን ናሙና በመውሰድ በመስክ ማመሳከር፤
5. በየደረጃው የኦዲት ክዋኔ ተግባቦትና ውይይቶች ማካሄድ፤

6. ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር መወያየት፤
7. መረጃ መተንተንና ሪፖርት ማዘጋጀት ናቸው፡፡

18.<u>የፕላን አፈፃፀም ክዋኔ ኦዲት ናሙና አወሳሰድ</u>

1. የመዋቅራዊ ፕላን ክዋኔ ኦዲት ሲደረግ እንደ ተተገበረው የቦታ ስፋት የአካባቢ ልማት ፕላን ካልተዘጋጀላቸው እና በቀጥታ መዋቅራዊ ፕላኑ ከተተገበረባቸው አካባቢዎች ከአምስት እስከ አስራ አምሰት ቦታዎች ላይ ናሙና በመውሰድ ወይም ከፊል ናሙና ወይም ችግር የታየባቸው ሳይቶችን በመለየትና ሁሉንም የመሬት አጠቃቀም ምድብ ያካተተ ይሆናል፤
2. የሰፈር ልማት ፕላን ያልተዘጋጀላቸውና በሽንሻኖ ፕላን ለሚተገበሩ የመዋቅራዊ ፕላኑ የተተገበረባቸውን ከመሀል የከተማው ክፍሎች እና ከማስፋፊያ አካባቢዎች ከእያንዳንዳቸው ከሦስት እስከ አምስት ወካይ ናሙና ሰፈሮች መምረጥና በተቻለ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ ሁሉንም የመሬት አጠቃቀም ምድብ ያካተተ እንዲሆን ማድረግ፤
3. የአካባቢ ልማት ፕላን በተዘጋጀላቸው አካባቢዎች ላይ የናሙና አወሳሰድ ከአጠቃላይ  የቦታው ስፋት ከ 30 በመቶ ማነስ የለበትም፤
4. በቢሮ ውስጥ በሚደረግ የፕላን ክዋኔ ኦዲት ላይ የናሙና አወሳሰድ በአጠቃላይ አገልግሎት ከተሰጠባቸው መረጃዎች ውስጥ ቢያንስ 35% መሸፈን ይኖርበታል፤
5. በተወሰደው ናሙና ላይ የተገኘው ችግር ስፋት ያለው ሆኖ ከተገኘ አገልግሎት የተሰጠባቸውን መረጃዎች ሙሉ በሙሉ በኦዲት ሥራው ሊሸፈኑ ይገባል፡፡

19.<u>የፕላን ክዋኔ ኦዲት ይዘት</u>

የፕላን ክዋኔ ኦዲት ይዘት የሚከተሉት ዋና ዋና የኦዲት ተግባራት ሊያካትት ይገባል፡-

1. የአካባቢ ልማት ፕላኖች የተተገበሩት ሳይቶች ወይም ሠፈሮች መካከል ናሙና በመውሰድ ኦዲት ማድረግ፤
2. ለአገልግሎት የዋለው መሬት ከፀደቀው የመሬት አጠቃቀም ፕላን ጋር ተገናዝቦ የተከናወነ ስለመሆኑ ማጣራትና ለዚህም ይረዳ ዘንድ የመሬት አጠቃቀም ካርታውንና የማጠቃለያ ሪፖርቱን በማየት ግንዛቤ መያዝ፤
3. በከተማው የሚተገበሩ የአካባቢ ልማት ፕላኖች የብሎክ የሽንሻኖ ስታንዳርድና ዲዛይን መሰረት በትክክል ወደ መሬት መውረዳቸውን ማመሳከር፤
4. የመሬት አጠቃቀም ለውጦችን ተጠንተውና አግባብ ባለው አካል ህግና መመሪያ

መሰረት ተፈቅደው መፈፀማቸውን ሰነዶችን መመርመር፤

5. በከተማው ውስጥ የተገነቡ መንገዶች በፕላኑ መሠረት መተግበራቸውን ማጣራት፤
6. በየዓመቱ የፕላን አፈፃፀም እቅድና ክንውን በእያንዳንዱ የመሬት ምደባ ዘርፍ መኖሩን ማጣራት፤
7. የከተማ የፊዚካል ወይም ገጸ ምድራዊ እና ሶሺዮ-ኢኮኖሚ ፕላን መረጃ አያያዝና አደረጃጀት በዘመናዊ የጂ.አይ.ኤስ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዳታ ቤዝ ወይም መረጃ ቋት በጥራት መደራጀቱን ማረጋገጥ፤
8. በፕላን አፈፃፀም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች የክህሎትና አቅም፣ አስፈላጊ የፕላን ማስተግበሪያ ዘመናዊ መሳሪያዎች በተገቢው የሙያ መሟላታቸውን መመርመር፤
9. ለፕላን ዘመኑ የሚያገለግሉ የቅየሳ መቆጣጠሪ ነጥቦች በትክክለኛው የፕላኑ አመላካች ልኬት በመሬት ላይ መተከላቸውንና ሳይነቃቀሉ መገኘታቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 20.<u>የድህረ ፕላን ክዋኔ ኦዲት ሥራዎች</u>

በኦዲት ስራ ማጠናቀቂያ ወቅት የሪፖርት፣ የመዝጊያና የክትትል ተግባር እንደሚከተለው ይከናወናል፡-

1. የኦዲት ምርመራው ውጤት ከኦዲቱ ዓላማ እና ወሰን አንጻር መከናወኑን ማረጋገጥ፤
2. የመጀመሪያ ደረጃ የኦዲት ግኝት ዘገባ ሪፖርት በመስክ ማጠናቀር፤
3. በኦዲት ግኝቱ መነሻነት በየደረጃው ከሚገኙ የፕላን ፈፃሚ ተቋማት አመራር አካላት፣ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር የመዝጊያ ውይይት ማካሄድ፤
4. በፕላን ክዋኔ ኦዲት ግኝት ላይ ወይም ኦዲተሮቹ በተከተሉት ስልት ኦዲት ተደራጊውያልተስማማባቸው ነጥቦች እንዲሁም የሚያነሷቸው ምክንያቶችን በቃለ-ጉባኤ መያዝ ናቸው፡፡

## 21.<u>የፕላን ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ይዘትና ቅርፅ</u>

የፕላን ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ይዘት የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል፡-

1. መግቢያ፣ ዓላማ፣ የኦዲት ምርመራው ወሰን፤
2. የፕላን ክዋኔ ኦዲት ውጤት ግኝቶች፤
3. መደምደሚያዎችን፣ አስተያየቶችን እና የማሻሻያ ሀሳቦች፤

4. በእያንዳንዱ የምርመራ ስራ ገፅ ላይ ፊርማ መፈረም፤
5. የፕላን ክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው የፕላን አፈፃፀም የጊዜ ወሰን፤
6. የፕላን ክዋኔ ኦዲት ቡድኑ አባላት ስም፣ ሪፖርቱ የተዘጋጀበት ቀን፡፡

22.<u>ስለ ከተማ ፕላን ኦዲት ሪፖርት አቀራረብ ሂደቶች</u>

በኦዲት ሪፖርቱ አቀራረብ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሂደቶችን መከተል ይኖርበታል፡-

1. የኦዲት መዝጊያ ስራው እንደተጠናቀቀ ዝርዝር ሁኔታዎችን ያካተተ ሪፖርት በማዘጋጀት ለፕላን አፈፃፀም የስራ ክፍል ማቅረብ፤
2. በሚመለከተው አካል የፀደቀውን የማጠቃለያ ሪፖርት ለኦዲት ተደራጊው እና ለሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መላክ፤

23.<u>ከኦዲት ግኝት ሪፖርት በኋላ ስለሚደረግ ክትትል</u>

በቢሮው ገጸ ምድራዊ ፕላን አፈጻጸም ክትትል እና ቁጥጥር ዘርፍ ውስጥ የፕላን አፈጻጸም ኦዲት ዳይሬክቶሬት ፡-

1. የኦዲት ስራው በተከናወነበት ፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈፃሚ ተቋም የሚገኘው የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ የስራ ክፍል በኦዲት ግኝት ሪፖርቱ መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን እስከ 6 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ኦዲቱን ላከናወነው ተቋምና በየደረጃው ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል፤
2. የፕላን አፈፃፀም ኦዲት ግኝቱ በሚጠቁመው ልክ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምት እንዲወሰድና በኦዲት ሪፖርቱ አግባብ ስለመስተካከሉ ኦዲት ያደረገው አካል ይከታተላል ወይም የክትትል ስራዎችን ያደርጋል፤
3. ኦዲት ያደረገው አካል የተወሰደው እርምት የተፈለገውን ውጤት ማስገኘት ስለመቻሉ መገምገም ይኖርበታል፡፡

24.<u>ጥቆማ፣ አቤቱታና የፍትሕ አካላት ማጣሪያ ትዕዛዝ</u>

የፕላን አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ሥራን ስኬታማ ለማድረግ፣ ከህዝብ ከሚመጣ ጥቆማና ከባለጉዳዮች አቤቱታ እንዲሁም የዳኝነት እና ሌሎች የፍትሕ አካላት ከሚሰጧቸው የፕላን ማጣሪያ ትዕዛዞች መረጃ በመጠቀም የክትትል እና ቁጥጥር ስራ በቢሮው ሊካሄድ ይችላል፡፡

25.<u>ከህብረተሰቡ ስለሚቀርብ የፕላን ጥሰት ጥቆማ</u>

1. በቀላሉ ተደራሽ የሚሆኑ የመረጃ መቀበያ ዘዴዎችን በመጠቀም የፕላን አፈፃፀምን የሚመለከቱ መረጃዎች ከህዝብ ጥቆማዎች ተሰባስበው ይደራጃሉ፤ በግብዓትነት ተተንትነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፤
2. የጥቆማ መቀበያ ዘዴዎች ድረ-ገፅ፣ ስልክ፣ አጭር ጽሑፍ መቀበያ መስመር፣ የሐሳብ መስጫ ሳጥን፣ የገፅ ለገፅ ግንኙነት እና ሌሎችም አግባብነት ያላቸው የተግባቦት መንገዶችን እንዲያካትቱ ይደረጋል፤
3. በማንኛውም መንገድ በፕላን ጥሰት ላይ የቀረቡ ጥቆማዎችን ቢሮው በማጣራት ለጠቋሚው አካል ጥቆማው በቀረበበት የመገናኛ ዘዴ ወይም ተግባቦት ዘዴ ውጤቱን የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤
4. በቢሮው የሚገኙትን እና በመስክ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከተገኘው የጥቆማ መረጃ ጋር በማገናዘብ ማጣራት ይደረጋል፤ የተገኘው ትክክለኛ ውጤት ለጠቋሚው እንደአስፈላጊነቱ በደብዳቤ ወይም በቃል ይገለፃል፤
5. ጥቆማ የቀረበበት ጉዳይ የፕላን ጥሰት ሆኖ ከተገኘና ጥቆማው ከመቅረቡ በፊት በቢሮው ያልተደረሰበት ከነበረ፣ ለጥቆማ አቅራቢው ማበረታቻ ሊደረግለት ይችላል፡፡

26.<u>አቤቱታ</u>

1. በፕላን አዘገጃጀትም ሆነ አፈፃፀም ሂደት መብቴ ተነክቷል ብሎ በሚቀርብ የባለጉዳይ አቤቱታ መነሻ በቢሮው በሚደረግ ማጣራት መሰረት የመብት መጓደል ወይም የፕላን ጥሰት መኖሩ ሲረጋገጥ፣ በሕግ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፤
2. የተወሰደው የማስተካከያ እርምጃ እንደ የአግባቡ ለሚመለከታቸው አካላት እና ለባለጉዳዩ በፅሑፍ እንዲገለፅ ይደረጋል፡፡

27.<u>የዳኝነት ወይም የሌላ የፍትሕ አካል ትዕዛዝ</u>

1. በዳኝነት ወይም በሌላ የፍትሕ አካል በሚሰጥ የፕላን ማጣሪያ ትዕዛዝ መሰረት በቢሮው አስፈላጊ ምርመራ ተደርጎ በሚገኘው ውጤት መሰረት ተገቢው ምላሽ ይሰጣል፤ የመብት መጓደል ወይም የፕላን ጥሰት መኖሩ ሲረጋገጥም፣ በሕግ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፤
2. የተወሰደው የማስተካከያ እርምጃ እንደ የአግባቡ ለሚመለከታቸው አካላት እና ለባለጉዳዩ በፅሑፍ እንዲገለፅ ይደረጋል፡፡

## 28.የመስክ ጉብኝት በማድረግ የሚሰባሰቡ መረጃዎች

በፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈፃሚ አካላት ለበቢሮው በተላኩ መረጃዎች እና/ወይም ቢሮው ዘንድ ባሉ የፕላን መረጃዎች እንዲሁም ከፕላን ክዋኔ ኦዲት ስራ በሚገኙ መረጃዎች መካከል አለመጣጣም መኖሩ ሲረጋገጥ፡-

1. በቢሮው በሚደረግ የመስክ ጉብኝት ምልከታ ውጤት መሰረት እንዲጣራ እና እውነታው ተለይቶ እንዲታወቅ ይደረጋል፤ የመብት መጓደል፣ የፕላን ጥሰት ወይም የግልፅነት ችግር መኖሩ ሲረጋገጥም፣ በፕላኑ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፤
2. በየስድስት ወሩ በሚወርድ የሳተላይት መረጃ እና በፕላን ክዋኔ ኦዲት ሥራ በተገኘ መረጃ፣ ከህዝብ ጥቆማ፣ ከአቤቱታ እና ከዳኝነት ወይም ከሌሎች የፍትሕ አካላት የማጣሪያ ትዕዛዞችም ሆነ ቢሮው ዘንድ በሚገኝ ሌላ መረጃ መሰረት ያለውን የፕላን አፈፃፀም ተጨባጭ ሁኔታ በመስክ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለማወቅ እንዲቻል የመስክ ጉብኝት ምልከታ በቢሮው ይደረጋል፤
3. የመብት መጓደል፣ የፕላን ጥሰት ወይም የግልፅነት ችግር መኖሩ ሲረጋገጥም፣ በፕላኑ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ቢሮው ይወሰዳል፡፡

# ክፍል ሦስት

# ስለክትትልና ቁጥጥር

## 29.በመዋቅራዊ ፕላኑን መሠረት ተደርጎ የተላለፉ ቦታዎች

1. በምትክ፣ በምደባ፣ በሊዝ ጨረታ፣ በሰነድ አልባ ይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በይዞታ መቀላቀል፣ በይዞታ ማካፈል፣ በይዞታ ላይ ማካተት እና በሌሎች ልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም በከተማው አስተዳደር ውሳኔ የተላለፉ ቦታዎች የማስተላለፍ አፈፃፀም በማጠቃለያ ሰነዱ እንዲሁም በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያም ሆነ አግባብ ባላቸው የመዋቅራዊ ፕላኑ ሌሎች ክፍሎች መሠረት ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፤
2. በፕላን ክትትልና ቁጥጥር ሂደት፡-
   ሀ) ማንኛውም የይዞታ ማረጋገጫ ቤዝማፕ መረጃ በሰነድና በኤሌክትሮኒክስ ቅጅ ከሚመለከተው ፕላን ፈፃሚ አካል እንዲመጣ ይደረጋል፤
   ለ) የተላከው የይዞታ ማረጋገጫ ቤዝማፕ በ2003 ዓ/ም በተወሰደው የመስመር ካርታ መሰረት ተደራጅቶ የተላከ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፤

ሐ) የተላከው የይዞታ ማረጋገጫ ቤዝማፕ የተሰጠበትን የፕላን መረጃ በ1988 ጅአይኤስ፣ በ1997 ዓ/ም የመስመር ካርታ ወይም ከነዚህ ከሁለቱ መረጃዎች ውጭ የተላለፈ አለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

3. በመዋቅራዊ ፕላኑ የመሬት አጠቃቀም መሠረት ለተሰጡ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃዶች፣ የሕንፃ አጠቃቀም ወይም የአገልግሎት ለውጦች፣ የቅይጥ መኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምጣኔ እና ሌሎች ጉዳዮች በማጠቃለያ ሰነዱ እንዲሁም በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያም ሆነ አግባብ ባላቸው የመዋቅራዊ ፕላኑ ሌሎች ክፍሎች መሠረት ክትትልና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

30.<u>በአካባቢ ልማት ፕላን መሠረት ስለሚተላለፉ ቦታዎች</u>

1. በምትክ፣ በምደባ፣ በሊዝ ጨረታ፣ በሰነድ አልባ ይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ በተያዙ ይዞታዎች መስተንግዶ፣ የሚካፈሉ ወይም የሚቀላቀሉ ይዞታዎች እና ሌሎች በከተማው አስተዳደር ውሳኔ ለባለይዞታ የተላለፉ ቦታዎች አግባብ ባለው የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም አግባብ ባላቸው የመዋቅራዊ ፕላኑ ክፍሎች መሠረት እንደአግባቡ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፤

2. የአካባቢ ልማት ፕላኑ እስከ ሸንሻኖ ፕላን የተዘጋጀ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩት ተግባራት አፈፃፀም በአካባቢ ልማት ፕላኑ ሸንሻኖ ፕላን መሠረት ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፤

3. የአካባቢ ልማት ፕላን እስከ ሸንሻኖ ፕላን ወይም የከተማ ንድፍ ፕላን የተዘጋጀለት ይዞታን ማካፈል የተከለከለ ነው፤

4. የአካባቢ ልማት ፕላን ባልተዘጋጀባቸው እና አካባቢ ልማት ፕላኑ እስከ ሸንሻኖ ፕላን ባልተዘጋጀባቸው አካባቢዎች አንድ ይዞታ ለሁለትና ወይም ከዚያም በላይ ሆኖ በሚካፈልበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ የይዞታ መጠን ቢያንስ በአካባቢው ያለውን አነሰተኛ ጥቅል ወለል ምጣኔ ወይም የሕንፃ ከፍታ ሊያስገነባ የሚችል መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፤

5. በአካባቢው ያለውን የህንፃ ከፍታ የሚያስገነባ አነስተኛው የቦታ ስፋት በሚዘጋጅ በህንፃ ከፍታ ዞን መሰረት መሆኑ ይረጋገጣል፤

6. ይዞታዎች በሚቀላቀሉበት ወይም በሚካተቱበት ጊዜ የሚቀላቀሉት ወይም

የሚካተቱት ይዞታዎች አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የመሬት አጠቃቀም ሊኖራቸው ይገባል፤

7. በመቀላቀሉ ወይም በማካተቱ ሂደት ለማምረቻ እና ለማከማቻ የመሬት አጠቃቀም ከቀለበት መንገድ ውስጥ እና ከቀለበት መንገድ ውጭ በሚል ከተቀመጠው የቦታ ስፋት መጠን በላይ መሆን እንደሌለበት ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡

31.<u>የግንባታ ፈቃዶች ክትትል</u>

የተሰጡ ግንባታ ፈቃዶችን በተመለከተ በሚከተሉት ላይ በፕላኑ መሰረት ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡-

1. የፕላን ስምምነት ማስረጃዎች፣ የመጠቀሚያ ፈቃዶች እና የሥራ ወይም የንግድ ፈቃዶች ፕላኑን ጠብቀው የተሰጡ መሆናቸውን፡-
   ሀ) የተሰጡ የፕላን ስምምነቶች በየደረጃው ያሉ ፕላኖችን መሰረት በማድረግ የተሰጡ መሆን አለባቸው፤
   ለ) የመጠቀሚያ ፈቃዶች በአንድ ይዞታ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን የመኖሪያ ቤት ምጣኔን፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ምጣኔን፣ የአረንጓዴ ቦታ ምጣኔን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መሆናቸውን፤
   ሐ) የስራ ወይም የንግድ ፈቃዶች ሲሰጡ በፕላን በተፈቀዱ ቦታዎች ላይ ብቻ መሆናቸው ማለትም የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን እና የመኖሪያ ቤት ምጣኔን ጠብቀው የተሰጡ መሆናቸውን፤
2. ለማናቸውም አይነት ግንባታ የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ አግባብ ባለው ፕላን መሰረት የተሰጠ መሆኑንና ግንባታውም በተፈቀደው መሰረት መከናወኑን በተለይም፡-
   ሀ) የተላከው የግንባታ ፈቃድ መረጃ በ2003 ዓ.ም የመስመር ካርታ መሰረት የተደራጀ መሆኑን፤
   ለ) የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ የህንፃ ከፍታን፣ በመንገዱ እና በግንባታው መካከል ያለውን እርቀት፣ በህንፃ ደረጃ ያለውን የመኖሪያ ቤት ምጣኔ፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ምጣኔ፣ የአረንጓዴ ቦታ ምጣኔ፣ የአቪኤሽን ዞን ክልከላ ወሰን፣ የወለል ምጣኔ በስታንዳርዱ መሰረት የተዘጋጁ መሆናቸውን፤
3. ለመሠረተ ልማት ዝርጋታ የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ፣ በመሬት ላይ፣ በመሬት

ውስጥ እና ከመሬት በላይ ያሉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ የያዘ መሆኑን፤

4. ማንኛውም የመሠረተ ልማት ገንቢ ወይም አስገንቢ ግንባታ በሚያካሂድበት ጊዜ ቀድመው የተገነቡትን መሠረተ ልማቶች በማይጎዳ መልክ መገንባት ያለበት ሆኖ፣ በግንባታ ወቅት ጉዳት የሚደርስባቸው የመሠረተ ልማቶች ካሉ ጉዳት ያደረሰው ተቋም ቀደም ሲል በነበረው ሁኔታ መልሶ መገንባቱንና አስተካክሎ መጠገኑን፡፡

32.<u>ከይዞታ ውጭ  እና ያለፈቃድ የተገነቡ ግንባታዎች</u>

1. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በተያዙ ይዞታዎች መስተንግዶ የሕግ ማዕቀፍ መሰረት ይዞታቸው ሕጋዊ የተደረገላቸው በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሰረት ተደርጎ ስለመሆኑ ቁጥጥር መደረግ አለበት፣
2. በይዞታ ውስጥ ወይም ከይዞታ ውጭ ያለግንባታ ፈቃድ የተሰሩና ፕላን የጣሱ ግንባታዎች ባለቤቶች በመዋቅራዊ ፕላን አዋጁ መሠረት ተጠያቂ ስለመደረጋቸው ቁጥጥር መደረግ አለበት።

33.<u>የመሠረተ ልማት ግንባታዎች</u>

የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን በተመለከተ ፡-

1. የመሠረተ ልማት ግንባታ ፈቃድ በማውጣት አግባብነት ባለው ፕላን እና በተሰጠው የግንባታ ፈቃዱ መሠረት ስለመከናወኑ፤
2. የመንገድ መሠረተ ልማት ዝርዝር ዲዛይን ሲዘጋጅ ከመንገድ ጋር ተያያዥ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ከሚመለከታቸው ፕላን ፈፃሚ አካላት ጋር በተቀናጀ መልኩ በፕላኑ መሠረት መከናወኑ ወይም እንዲከናወን ስለመደረጉ፤
3. የውሃና የፍሳሽ መስመር፣ የኤሌክትሪክ መሰመር፣ የስልክ ወይም ሌሎች የመገናኛ መስመሮችን የሚገነቡ ተቋማት መንገድን ተከትለው ለሚሰሯቸው ሥራዎች በዕቅዱ  መሠረት አስቀድመው የመንገድ ዲዛይኑን ለሚሰራው አካል የማሳወቅ እና አስፈላጊውን መረጃ የመስጠት ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው እንዲሁም ለሥራውም ተባባሪ ስለመሆናቸው፣

ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

34.<u>የሕንፃ አጠቃቀም</u>

የሕንፃ አጠቃቀምን በተመለከተ፡-

1. ማንኛውም ሕንፃ በግንባታ ፈቃድ ፕላኑ በተመለከተው አጠቃቀም ወይም አገልግሎት መሠረት ብቻ ሥራ ላይ ስለመዋሉ፤
2. የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ በሚሰጥበት ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሚታደስበት እና የአገልግሎት ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ፣ በቅይጥ መኖሪያ የመሬት አጠቃቀም ምጣኔ መሠረት የተፈፀመ ስለመሆኑ፤
3. በማንኛውም ሕንፃ ላይ የሚሰጡ የሥራ ወይም የንግድ ፈቃዶች እንዲሁም የመሬት አጠቃቀም ወይም የአገልግሎት ለውጦች የሚያስከትሉት ማህበራዊ ቀውስ አለመኖሩ ስለመረጋገጡና በመዋቅራዊ ፕላኑ በተከለከሉ አገልግሎቶች ያልተካተቱ ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው የሚከተሉትን ያካትታል፡-
   ሀ) ከትምህርት ተቋማት 500 ሜትር ክብ ውስጥ መራቅ ያለባቸውን ጫት መሸጫ ቤቶች፣ የሸሻ ቤቶች፣ የማሳጅ ቤቶችን እና አገልግሎቶችን ፤
   ለ) የማህበረሰቡን ባህልና ወግ ለመጠበቅ ሲባል በዋና ማዕከል፣ በሁለተኛ ደረጃ ማዕከላት እና በዋና ዋና መንገዶች ላይ ብቻ የሚፈቀዱ አገልግሎቶች የምሽት ጭፈራ ቤቶች፣ ጫት መሸጫ ቤቶች እና ማሳጅ ቤቶችን፤
   ሐ) በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በቅይጥ መኖሪያ የመሬት አጠቃቀም ላይ የሚፈቀዱ ሆነው ነገር ግን የድምጽና የአቧራ ብናኝ ብክለት የሚያስከትሉ የመሬት አጠቃቀሞች ከግንባታእስከ አጠቃቀም ልዩ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግላቸው እንደ የወፍጮ ቤቶች፣ የተሽከርካሪ መጠገኛ ቦታዎች፣ የብረታ ብረት ሥራ ቦታዎች፣ የእንጨት ሥራ ቦታዎች፡፡

35.<u>በአረንጓዴ መሠረተ ልማት ቦታዎች ላይ የተሰሩ ዝርዝር ዲዛይኖች</u>

የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ቦታዎች ዝርዝር ዲዛይኖችን በተመለከተ በሚከተሉት ላይ በፕላኑ መሰረት ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡-

1. በመዋቅራዊ ፕላኑ የመሬት አጠቃቀም ምድብ የተሰጣቸው የአረንጓዴ ቦታዎች ከመልማታቸው በፊት ለልማታቸው የሚያስፈልግ ዝርዝር ዲዛይን አዘገጃጀት በቢሮው የፀደቀ መሆኑን፤
2. መካነ መቃብሮች በከተማው ውበት እና የዓይን መስህብነት እንዲውሉ ሲደረግ ፡-
   ሀ) በዲዛይን መሠረት ለተለያዩ አገልግሎቶች ከተያዙት ቦታዎች ውጭ የሚገኙ ክፍት ቦታዎች ሁሉ በአረንጓዴ ዕፅዋት መሸፈናቸውን፤

ለ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ ውስጥ በሚገኙ መንገዶች ግራና ቀኝ በየ5 ሜትሩ የጥላና የውበት ዛፎች መተከላቸውን፤

ሐ) በዘላቂ ማረፊያ ግቢ ውስጥ ለአረንጓዴ ልማት የሚተከሉት ዕፅዋት በሚዘጋጀው የላንድስኬፕ ጥናት መሠረት የሚመረጡ ሆኖ ዕይታን የማይጋርዱ፣ ውበት የሚፈጥሩ ስሮቻቸው በመቃብርና በግንባታዎች ላይ ጉዳት የማያስከትሉ፣ በእርጥበትና በጥላ የተነሳ በመቃብሮችና በሌሎች ግንባታዎች ላይ የመበስበስና የመሰነጣጠቅ አደጋዎች የማያስከትሉና አገር-በቀል ዕፅዋት በተመራጭነት የሚተከሉባቸው መሆናቸውን፤

መ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ ውስጥ በተመረጡ ቦታዎች ላይ ለጎብኝዎችና ለእንግዶች ማረፊያ የሚሆን ከእንጨት ወይም ከኮንክሪት የተሰሩ ወንበሮች መዘጋጀታቸውን፤

ሠ) የሚተከሉት ዕፅዋት ስብጥር ትልልቅ የጥላ ዛፎችን፣ የውበት ዛፎችን፣ ቁጥቋጦዎችን እና ለንፋስ መከላከያነት የሚያገለግሉ ተክሎችን ማካተቱን፤

ረ) በዘላቂ ማረፊያ ምድረ-ግቢ ውስጥ የሚገኙ ሳሮች፣ ቅጠላቅጠሎች፣ ዛፎችና ቁጠቋጦዎች በየወቅቱ መታጨድና መከርከማቸውን፤

ሰ) ዛፎችና ቁጥቋጦዎች በመቃብርና በአስተዳደር ሕንፃዎች ላይ ጉዳት ሊያመጡ በሚችሉበት ደረጃ ሲደርሱ ወይም የዘላቂ ማረፊያውን ውበት የሚያጎድፉ ሆነው ሲገኙ መወገዳቸውን፤

ሸ) በመቃብር ቦታዎች ለመታሰቢያ የተቀመጡ አበባዎች ውበታቸውን ከጨረሱ በኋላ መወገዳቸውን፡፡

## 36.<u>የቅርስ ቦታዎች እና ሕንፃዎች</u>

የቅርስ ቦታዎች እና ሕንፃዎችን በተመለከተ በሚከተሉት ላይ በፕላኑ መሰረት ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡-

1. የከተማው መዋቅራዊ ፕላን ባስቀመጠው የቅርስ ቦታዎች በሆኑ ታሪካዊ ስፍራዎች እና ግንባታዎች አያያዝና አጠባበቅ መሠረት ክትትልና የቁጥጥር አፈፃፀሙ በከተማ ፕላን አሰራር ደንቦች ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ፤
2. በከተማው ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች በመዋቅራዊ ፕላኑ ለቅርስ ቦታዎች እና ሕንፃዎች የተቀመጠውን ደረጃ በጠበቀ መልኩ ስለመፈፀሙ።

37. <u>ስለ ክትትልና ቁጥጥር አመራር</u>

ቢሮው የፕላን አዘገጃጀት፣ አፈፃፀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር ለመምራትና በስኬታማነት ለማቀላጠፍ ገፀ-ምድራዊ ፕላንን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራትን ያከናውናል፡-

1. የተጣጣመ፣ የተደጋገፈና ተጠያቂነት ያለበት የመዋቅራዊ ፕላኑ ክፍሎች ትግበራ ዝርዝር አፈፃፀም መኖሩን ማረጋገጥ፤
2. የፕላን ዝርዝር አፈፃፀም ከማጠቃለያ ሰነዱ ጋር የተገናዘበ እንዲሆን ማድረግ፤
3. በመዋቅራዊ ፕላን እና በአካባቢ ልማት ፕላን መካከል ልዩነት ሲያጋጥም፣ የመዋቅራዊ ፕላኑን ገዢ ተፈፃሚነት ማረጋገጥ፤
4. የአካባቢ ልማት ፕላን ባልተዘጋጀላቸው የከተማው አካባቢዎች መዋቅራዊ ፕላኑን በቀጥታ ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉን ማረጋገጥ፣ እና አግባብ ያላቸው ቅድመ ሁኔታዎችን ማማቻቸት፤
5. መዋቅራዊ ፕላኑ የመሬት አጠቃቀም ምድቦች ያልተመላከቱ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀሞች እንደ የአግባቡ በአካባቢ ልማት ፕላን ወይም በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያ በተወሰነው መሠረት ተለይተው ለአገልግሎት እንዲውሉ መደረጉን ማረጋገጥ፤
6. በግንባታ ፈቃድ መሠረት ግንባታ እንዲካሄድ መደረጉንና ያለግንባታ ፈቃድ የተካሄደ ግንባታም በሕግ መሠረት ፈቃድ እንዲኖረው ወይም እንዲወገድ መደረጉን ማረጋገጥ፤
7. ለፕላን አፈፃፀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ፕላኖችን፣ ዲዛይኖችን፣ ስታንዳርዶችን፣ ግንባታ ፈቃዶችን፣ የይዞታ ካርታዎችን፣ የፕላን ስምምነት ሰነዶችን፣ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃዶችን፣ ፕሮጀክቶችንና ተዛማጅ ሰነዶችን እንዲሁም ሌሎች አግባብ ያላቸው መረጃዎችን ከተለያዩ ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት መሰብሰብ፣ በስርዓት አደራጅቶ መሰነድና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤
8. በፕላን መሠረት በትክክል የተሰጡ አገልግሎቶች በቤዝ ማፕ የመረጃ ቋት እንዲደራጁ ማድረግ፤
9. ከፕላን ፈፃሚ አካላት ጋር ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤
10. በፕላን አስፈፃሚ አካላት በሚላኩ መረጃዎች መሠረት ዕለታዊ የሆነ የፕላን

አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እና የተገኙ የፕላን ጥሰቶች እንዲስተካከሉ ማድረግ፤

11. የመስክ ምልከታ በማድረግ የዋና ዋና ፕሮጀክቶች፣ የሕንፃዎች፣ የክፍትና የአረንጓዴ ቦታዎች፣ አጠቃቀም፣ ደረጃ አጠባበቅ ሁኔታዎችንና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፕላን አፈፃፀም አኳያ በየወቅቱ ቅኝት ማድረግ እና የሚታዩ የፕላን ጥሰቶች እንዲስተካከሉ ማድረግ፤
12. በፕላን ፈፃሚ ወይም አስፈጻሚ የከተማው አስተዳደር አካላት ላይ የፕላን ትግበራ ወይም የክዋኔ ኦዲት ሥራ ማካሄድ፣ በኦዲት ግኝቶች ሪፖርት መሠረት ማስተካከያዎች እንዲደረጉ ለሚመለከተው አካል በፅሑፍ ማሳወቅ እና መስተካከላቸውን ማረጋገጥ፤
13. የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ ባነሮች ወይም ጽሑፎች የሚተከሉባቸው ወይም የሚለጥፍባቸው ቦታዎች፣ ግንባታዎችና ሌሎች ቋሚ መሰረተ ልማቶች ደረጃ ማዘጋጀት እና በፀደቀ ደረጃ መሠረት እየተፈፀሙ መሆናቸውን በመከታተል እና በመቆጣጠር እንዲፈፀም ማድረግ፤
14. በፕላን አዘገጃጀት፣ አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ሂደት የሚታዩ የአሰራርና የግንዛቤ ክፍተቶችን፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ስህተቶችን ከግምት በማስገባት የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 38. ስለተጠያቂነት

የዚህን መመሪያ አፈጻጸም ያሰናከለ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 39. መመሪያውን ስለማሻሻል

ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

### 40. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ቢሮው ያወጣው መመሪያ፣ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 41. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

*ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው ድረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡*

**አዲስ አበባ ግንቦት 2017ዓ.ም**

**ዳዲ ወዳጆ (ዶ/ር)**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ**